# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)
# የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ፕሮግራም

## SSL ምንድነው?

- የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ማለት ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል መካከል ለሚገኙ ተማሪዎች የስቴት የመመረቂያ መስፈርት/መመዘኛ ነው።
- ተማሪዎች ለማህበረሰቡ በበጎፈቃደኝነት በሚያበረክቱት አገልግሎት ትርጉም ያለው ትምህርት ያገኛሉ።
- የአገልግሎት ትምህርት ስለ ዜጎች/የዜግነት እዉቀት፣ ስለዜጎች ተሳትፎ፣ ስለአካዴሚያዊ ስኬት፣ እና የተማሪዎች ባህርያዊ እና ማህበራዊ እድገትን ያዳብራል/ያበረታታል።
- ቤተሰቦች እና ተማሪዎች የ MCPS SSL ሪሶርሶች ማዕከልን ይመልከቱ http://bit.ly/SSLHubMCPS እና ይህን ስለ SSLፕሮጀክት ናሙና የሚያስረዳ ቪድኦ ይመልከቱ http://bit.ly/mcpssslvideo!

## የሜሪላንድ (MD) ስቴት እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመዘኛዎች-መስፈርቶች

- የሜሪላንድ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በሙሉ ሰባአምስት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት "75 SSL hours" ሠአት ያገኛሉ።
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች 5ኛ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ **ካለው የሠመር ወቅት ጀምሮ ለመመረቂያ** አስፈላጊ የሆነ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓት ለማግኘት መሥራት ይችላሉ።
  ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከሚጨርሱ ድረስ እየሰሩ ሠዓት ማጠራቀም ይችላሉ።
- ከ 6ኛ ክፍል በኋላ በ MCPS የተመዘገቡ ተማሪዎች SSL መስፈርት የሚያካክስ እፎይታ ያገኛሉ።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓት እንዴት ለማግኘት ይችላሉ?

ተማሪዎች ለምረቃ የሚያስፈልገዉን "75 SSL ሰአታት" ለማግኘት የሚችሉት በሁለት መንገድ ነው:-

1. **ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ኮርሶች በስኬታማነት ሲያጠናቅቁ ሃምሳ SSL ሠዓቶችን "50 SSL hours" ለማግኘት ይችላሉ። በክፍል የምርምር እና የአገልግሎት ፕሮጀክቶች መምህራን ሊመሯቸው ይችላሉ።**

| | |
|---|---|
| 10 ሠዓት | 6ኛ ክፍል ሳይንስ/Science |
| 10 ሠዓት | 7ኛ ክፍል እንግሊዝኛ/English |
| 10 ሠዓት | 8ኛ ክፍል ማህበራዊ ጥናት/Social Studies |
| 5 ሠዓት | ሁ/ደ/ት/ቤት የጤና ትምህርት B/Health B |
| + 15 ሠዓት | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ብሔራዊ፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር |
| **50 ሠዓት በአጠቃላይ በትምህርት ቤት የክፍል - ትምህርቶች** | |

2. **የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ከትምህርት ቤት ውጪ (ለትርፍ ያልተቋቋሙ ኤጀንሲዎች)**
   ተማሪዎች Montgomery County Volunteer Center (MCVC) ድረ-ገጽ በመጎብኘት MCPS SSL ድርጅቶችን እድል ለማግኘት ይችላሉ (www.montgomeryserves.org) ተቀባይነት ያላቸው SSL እድሎች። (ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሁሉም የመመረቂያ ቆብ እና "MCPS SSL" ምልክት/አርማ ይኖራቸዋል። እባክዎ አባሪ በተደረገው ጽሑፍ ላይ MCVC ድረ-ገጽ በመፈለግ ፍንጭ ያግኙ።)

   እንዲሁም ተማሪዎች MCVC ድረገጽ ላይ ያልተመዘገቡ እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ኤጀንሲዎችን (ኃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ኤጀንሲዎች ወይም ተቋማትን በራሳቸው መፈለግ እና ቅጽ **"MCPS Form 560-50"** መሙላት ይችላሉ። **በግል የተማሪ አገልግሎት ትምህርት መጠየቂያ ቅጽ** (http://bit.ly/SSLPreApproval) ሞልተው ለት/ቤታቸው SSL አስተባባሪ (በትምህርት አመቱ) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤ ወይም ssl@mcpsmd.org (በሠመር ወቅት) አገልግሎት ከመጀመራቸው አስቀድሞ ውሳኔ እንዲሰጥ ማቀረብ አለባቸው።

## MCPS SSL እድሎች በሙሉ --- መሆን አለባቸው:-


- ለትርፋማነት ያልተቋቋመ የተመዘገበ ኤጀንሲ
- በህዝብ መገልገያ ቦታ
- ክትትል/ቁጥጥር ተደርጓል (በወላጅ ወይም በዘመድ አይደለም)
- ለበጎፈቃድ አገልግሎት ብቻ (የማይከፈልበት)
- በቀን 8 ሠዓት ያልበለጠ

**ለትርፍ ያልተቋቋመ የተማሪዎ አገልግሎት ትምህርት SSL እድል የሚሰጡ ኤጀንሲዎችን/ተቋማትን ለማግኘት እባክዎ ይህን በይነመረብ ይጎብኙ:-**
https://bit.ly/SSLOpportunities

## MCPS Form 560-51: *የተማሪ አገልግሎት ትምህርት የተግባር ማረጋገጫ* https://bit.ly/SSLReflection

ይህ ቅጽ የተማሪን SSL ሰአት ለመመዝገብ እና በት/ቤት ለሚገኝ SSL አስተባባሪ የተማሪዎችን SSL ሰዓቶችን በማረጋገጥ ለመመዝገብ ጥቅም ላይ ይውላል። (የቅጹ መመሪያ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል https://bit.ly/SSLForm101)

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ SSL ሠዓት ለማግኘት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን ለመወሰን ይህንን የቅደም ተከተል ቻርት ስዕላዊ መግለጫ ይጠቀሙ።




## ልዩ SSL መመዘኛዎችን ለሚያሟሉ ተማሪዎች ሁለት (2) አይነት SSL ሽልማቶች ይኖራሉ።

| ክፍል | ሽልማት |
|---|---|
| 6ኛ፣ 7ኛ፣ እና 8ኛ ክፍሎች | **ስለ አገልግሎት ትምህርት ከሱፐርኢንተንደንት የሚሰጥ ሽልማት**<br>(በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለ(ች) የተገኘ 75 ሠዓት፣ አንድ ጊዜ ብቻ የተሰጠ) |
| 12ኛ ክፍል | **ሽልማት የሚገባው አገልግሎት ሠርተፊኬት/በችሎታ የሚሰጥ አገልግሎት ሠርተፊኬት**<br>(በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመመረቂያ/ሲንየር ዓመት የተገኘ 240 ሠዓት) |

**<u>የተማሪ አገልግሎት ትምህርት SSL ቅጾች በሙሉ</u>** በወቅቱ የትምህርት አመት እና የትምህርት አመቱ በተጠናቀቀበት የሠመር ወቅት ተሞልተው **<u>መቅረብ አለባቸው</u>** ቅጾቹ ተሞልተው ለት/ቤት SSL አስተባባሪ መቅረብ ያለባቸው **<u>ሜይ ወር ከመጨረሻው ዓርብ በፊት ነው።</u>**

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃደኞች ማዕከል ድረ-ገጽ፡** www.montgomeryserves.org

**MCPS SSL ድረ -ገጽ፡** www.mcps-ssl.org

**ይከታተሉ! @mcps_ssl**

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማእከል (MCVC)
# ለተማሪዎች የአገልግሎት ትምህርት እድሎች እና ድርጅቶችን መፈለጊያ ድረ ገጽ





## MCPS SSL የተማሪ አገልግሎት ትምህርት እድል መፈለጊያ





__መጀመሪያ 1፡__ ይህን ድረገጽ ይክፈቱ፡- www.montgomeryserves.org.
በገጹ ላይ ቀዩን ምልክት “MCPS SSL Opportunities” ጠቅ ያድርጉ።


__ሁለተኛ 2፡__ የአገልግሎት መስጫ እድሎችን ለመፈለግ እና/ወይም ለማጣራት የመረጃ መረብ መፈለጊያ "Search Tools" ይጠቀሙ፡-

- ቁልፍ ቃላትን በመጠቀም ለመፈለግ፣ በዚህ ክፍት ቦታ ላይ ቃሉን ይጻፉ (ለምሳሌ፡- hunger, children, animal ወዘተ)




- ዕድሎችን ለማጣራት፣ “Filter By” የሚለውን ይጠቀሙ፡-
(ያሉትን አማራጮች ዝርዝር ለማየት ሞባይል ወይም ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የሚጠቀሙ ከሆነ ይህንን ምልክት ጠቅ ያድርጉ 🔧)




እያንዳንዱ የዝርዝር ማጣሪያ የተለየ አሠራር አለው።

የሚፈልጉትን እድል እስከሚያገኙ ድረስ ማጣሪያ ቃሉን እየጻፉ ማሰስ ይቻላሉ!

__ሦስተኛ 3፡__ እርስዎ የሚፈልጉትን እድል ሲያገኙ በድረ-ገጹ ላይ በቀጥታ ፍላጎትዎን ለመግለፅ ይህን ምልክት 

ጠቅ አርገው በመክፈት ፍላጎትዎን መግለፅ ይችላሉ።


ለድርጅቱ በቀጥታ መደወል ወይም ኢሜል መላክ ከፈለጉ፣ ካሉት እድሎች መግለጫ በስተቀኝ ያለውን የድርጅቶች ዝርዝር ገጽ ላይ ጠቅ በማድረግ የስልክ ወይም የኢሜል አድራሻቸውን ማግኘት ይችላሉ።

# MCPS SSL የተማሪ አገልግሎት ትምህርት እድል የሚሰጡ ድርጅቶችን ለመፈለግ


<u>ለመጀመር 1:</u> ይህንን ድረገጽ ይከፈቱ፡- www.montgomeryserves.org. በገጹ አናት ላይ “MCPS SSL Organizations” የሚለውን ቀይ ምልክት ጠቅ አድርገው ይከፈቱ።




<u>ሁለት 2:</u> ከመዳሰሻ ላይ “Filter By” የሚለውን መለያ በመጠቀም “Name” የሚለውን ይምረጡ።




<u>ሦስት 3:</u> በመዳሰሻው ሣጥን ላይ የድርጅቱን ስም ታይፕ ያድርጉ እና “Search” የሚለውን ጠቅ አድርገው ይከፈቱ።





<u>አራት 4:</u> ድርጅት/Organization የሚለው ገጽ ላይ ጠቅ አድርገው ይከፈቱ)። “What We Do” በሚለው ክፍል MCPS SSL ምልክት ካዩ)፣ በዚህ ድርጅት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ SSL ሠአቶችን ማግኘት ይችላሉ።




<u>አምስት 5:</u> ፖስት የተደረጉ ማናቸውንም ድርጅቶችን ለማየት ምልክቱን ወደታች መሸብለል ያስፈልጋል።

<u>ስድስት 6:</u> በዚህ ድርጅት በቅርብ ጊዜ የሚወጡ እድሎችን መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ይህን ምልክት ከፍተው ይመልከቱ።




# ቀን የተገለፀበትን የአገልግሎት እድል ለመፈለግ

<u>1ኛ</u> ይህን ድረገጽ ይከፈቱ፡- www.montgomeryserves.org. በተለያዩ ቀኖች-ያሉትን እድሎች ለማወቅ በገጹ አናት ላይ ያለውን ቀይ ምልክት “Calendar” ጠቅ በማድረግ ከፍተው ይመልከቱ።




<u>2ኛ</u> ዝርዝሮችን ለማየት "specific opportunity" የሚለውን ጠቅ አድርገው ይከፈቱ። ይህንን ምልክት/ባነር የተለያዩ እድሎች በተዘረዘሩበት ገጽ አናት ላይ ካገኙ በነዚያ እድሎች ላይ በመሳተፍ SSL ሰዓቶችን ማግኘት ይችላሉ፡-

